## ማን ያውራ የነበረ 1

ያልነበሩና ያላወቁ አልያም ቅን ቢሆኑም የተሳሳተውን አምነው የሚያወሩ በርከት ባሉበት በአሁኑ ወቅት ወይም ቅጥፈት ቤተ መንግስት ገብታ መለስ ዜናዊ የተባለን ባለሙያ አሰማርታ ባለችብት በአሁኑ ጊዜ ኢሕአፓ ላይ ልዩ ትኩረት ተደርጎ የስም ማጥፋቱ ዘመቻ እየተካሄደ በመሆኑ ማን ያውራ የነበረ በሚል አጠቃላይ ርዕስ ስር የድርጅቱን መሰረታዊ አቅዋሞች በተከታታይ እያብራራን እናቀርባለን። በዚህም ረገድ የድርጅቱን ታሪክ ባስፈለገበት መዳሰሳችንና ራዕዩና መርሁንም ማቅረባችን የግድ ይሆናል።

በመጀመሪያ ደረጃ ርዕሳችን አድርገን የወሰድነው ኢሕአፓና የኦሮሞ ሕዝብ ትግል የሚለውን ነው። ድርጅቱ አንድም የኦሮሞ ሕዝብን ትግል የተቃወመ አስመስለው የሚያቀርቡና የሚፅፉ ሲኖሩ በሌላ በኩል ደግሞ የአሮሞን ሕዝብ ትግል ከመደገፍም አልፎ የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባርን የመገንጠል ፐርግራም ሁሉ ደግፎ በአስመራ ከኦነግ ጋር እየተመሳጠረና እየሰራ ነው ብለው የሚከሱም አሉ። የኢሕአፓ አቅዋም የትኛው ነው?

ኢሕአፓ በምሰረታ ሂደቱ ወቅትና ከተመሰረተበት ከ 1964 ዓ.ም. ጀምሮ የጭቁን ሕዝብን የእኩልነት መብት በግልፅ ደግፎ የወጣ ድርጅት ነው። አብዛኛው የኦሮሞ ተወላጅ ደግሞ በባላባቱ ወይም ፊውዳሉ ስርዓት በነፍጠኝነት ተቀይዶና ማንነቱ ላይ ጥቃተ ደርሶበት መብት አልባ ሆኖ የሚማቅቅ ስለነበር ኢሕአፓ ለኦሮሞ ሕዝብ መብት ቆሟል፤ታግሏል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በአብዛኛው በአምባገነን ስርዓት ስር የነበረ ቢሆንም ብሄረሰቦች ደግሞ በተለየ ደረጃ የሚደርስባቸውን በደል ኢሕአፓ አበጥሮ በማቅረብ ይህም ጭቆና እንዲወገድና የሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብት በተከበረበት ሁኔታ የሀገር ዘላቂ አንድነት እንዲገነባ ታግሏል። የኦሮሞ ሕዝብን ኢትዮጵያዊነት ለሰኮንድም ቢሆን ያልተጠራጠረው ኢሕአፓ የሕዝቡን መብት የመንፈግ እርምጃ ሕዝብን እያገለለ ና እያራቀ እያቃረነ በመሄዱ ሀገርን ይጎዳል፤ መፈራቀቅን ያባብሳል ሲል ትምክህትን በታየበት ሁሉ ተቋቁሞታል። በርካታ የኦሮሞ ተወላጆች የኢሕአፓ መስራችም አባልም በመሆን ታግለው የከፈሉት መስዋዕትነት ለዚሁ ምስክር ነው። ዛሬ የኢሕአፓ ታሪክ ሲጠቀስ ታግለው የተሰዉለትን እነ ገመቹን፤ታየ ቶላን፤ ተስፋዬ ሁንዴን፤ ግርማ ቶሎሳን፤ካሳ ኩማን፤ አባስ ሙስጠፋን፤ወርዶፋ አያናን፤ፈቃዱ ገመዳን፤ታደለ ያደታንና ሺዎችን የኦሮሞ ተወላጆችን ስም፤ የጅማዎቹን፤ የሐረሮቹን፤ የሸዋዎቹን፤ የባሌዎቹን፤ ወዘተ መዘርዘር ከቶም የማይታለፍ ነው። ወታደራዊ መንግስት ለኦሮሞ ሕዝብ የመጣሁ ነኝ ብሎ ድጋፍን ሊያገኝ ሲሯሯጥም ኢሕአፓ ይህንን ፀረ ሕዝብ ስርዓት አወገዘና ታገለ እንጂ እወነትክን ብሎ አልደገፈውም፤ የሰደድ አባል፤ የቀበሌና የከፍተኛ የአብዮት ጥበቃ አባል ሆኖም በግፉ አልተባባረውም። በዚያን ወቅትም ቢሆን ኢሕአፓ የኦሮሞ ሕዝብ መብት ይከበር ብሎ ከመታገል ወደ ኋላ አላለም ነበር።

ኢሕአፓ ጭቁኑ ኦሮሞ መብቱን መቀዳጀት አለበት ብሎ በአጠቃላይም በሀገር አቀፍ ደረጃ ለዴሞክራሲ ከሚያካሂደው ትግል ጋር አቆራኝቶ ሲታገል ለኦሮሞ ሕዝብ መብት ቆሚያለሁ ብሎ ከተገኘው ከኦነግ መስመርና አቅዋም ጋር ግን መጣጣም አለመቻሉ ምስጢር አይደለም። ኢሕአፓ በአቅዋም ከኦነግ የተለየው ለምን ለኦሮሞ ሕዝብ መብት ቆሚያለሁ የሚል ድርጅት ተቋቋመ በሚል ሳይሆን ይህ ድርጅት የኦሮሞን ሕዝብ ኢትዮጵያዊነት በመሰረዝ ባዕድ ነን፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የምንዛመደው በአዳም ልጅነት ነው፣ በግድ ተገንጥለን ኦሮሚያን ማቋቋም አለብን ብሎና ወደ ጥበት ፅንፍም ተስፈንጥሮ በመገኘቱ ነው። የአሁኑ ኦነግ ገና ከምስረታውም ሻዕቢያ የጠላውን ጠልቶ በመነሳቱና ኢትዮጵያ ያለውን ሁሉ በአማራ ትምክህተኛነት በመፈረጁ ከኢሕአፓ ጋር ቀና ግንኙነትን ሊመሰርት አልቻለም ነበር። ከደርግ ዘመን የተቃራኒ ጎራዎች ሰልፍ ባሻገር ደግሞ ወያኔ ስልጣን ሲይዝ ሲዳዳ የኦነግ አመራር ከወያኔ መሰሪ ዕቅድ በተፃረረ መንገድ አቅዋም ማንፀባረቅ ባለመቻሉ አቶ ሌንጮ ለታ እንዳለው በሎንዶኑም የወያኔ ሻዕቢያና አሜሪካ የሰላም ጉባዔ ተብዬ በሽፋን ሲጪነት ደረጃ ተገኝቶ ነበር። ከዚያም በሽግግሩ ጉባዔ የወያኔ አምባገነንነት ግልፀ ሆኖ ሳለ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ለምን ታገዱ የሚልን ተቃወሞ ሳያነሱ የኦነግ መሪዎች የወያኔን መሰሪ ሂደት ተባብረው የወያኔ ጦር የሽግግሩ መንግስት ሰራዊት መሆኑን እከመቀበል ደረሱ ። ወያኔ የራሱን ፀረ ኦሮሞ ሴራ ከግብ ለማድረስ ኦሕዴድ የሚል ተለጣፊ አዘጋጅቶ እያለ የኦነግ አመራር ተገቢውን ግምገና አካሂዶ የሚያዛልቅ ዕቅድና ጥንቃቄ ሊኖረው አልቻለም። በሽግግሩ ወቅትም የተከሰቱት የእነ በደኖ ና አርባጉጉ ዓይነቶች አሶሳን ደጋሚ ፍጅቶች ለድርጅቱ ያስገጠለት ውጤት ጉዳትን አንጂ ጠቀሜታን አልነበረም። የኦነግ አመራር የኢትዮጵያን ሁኔታ በሚገባ ባመጤንና የብዙሀኑን የኦሮሞ ሕዝብ ፍላጎት በመመርመር ተገቢውን የአቅዋም ለውጥ በድፍረት ተቀብሎ በኢትዮጵያዊ ድርጅትነት የኦሮሞን ሕዝብ ኢትዮጵያዊነት በመቀበልና የመገንጠልን ፕሮግራም በመተው ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወት ሲችል አልፈለገም ወይም አልሆነለትም። ዛሬም ይህ ድክመት የኦነግን ችግር ገላጭ ሆኖ መገኘቱ አከራከሪ አይመስለንም።

ኢሕአፓ ኦነግን ሆነ ሌሎች ድርጅቶች ሲተች እነሱም በኢሕአፓ ላይ ያላቸው ትችት ያላቸው መሆኑን አጥቶት አይደለም። ሆኖም በድርጅት አቅዌሮም ላይ ያለ ሂስ በሕዝብ ትግል ላይ ሊለጠፍ ሰለማይችል ኦነግ ሆነ ሌላ መሰል ድርጅት ተወደደም ተጠላም የኦሮሞ ሕዝብ ለመብቱ የሚያደርግውን ትግል ኢሕአፓ ከመደግፍ ወደ ኋላ ብሎ አያውቅም። በአሁኑ ወቅት አንዳንዶች ለምን ኦነግ ከሻዕቢያ አበረ በሚል ሆነ አቅዋሙን ለምን አላስተካከለም በሚል ምክንያት የወያኔን ፀረ ኦሮሞ ዘመቻ ከማቅገዝ ሲቆጠቡም ኢሕአፓ ይህንን አቅዋም አወገዘ አንጂ ደግፎ የወያኔን ፀረ ኦሮሞ ዘመቻ ከማጋለጥ ወደ ኋላ አላለም።በፀረ ኦነግንት ሽፋን የሚውገረገረውን ፀረ ኦሮሞነት ታግሏል። ተቃዋሚ ነን እያሉ የመለስ ዜናዊን ፀረ ኦሮሞ እርምጃ የሚደግፉትን ወይም በትምክህት ተይዘው የሕዝብን እኩልነት የሚቃወሙትን ዛሬም ኢሕአፓ እየታገለ ነው። የኦነግን ባዕድ ነን፣መገንጠል አለብን አቅዋምን ብንቃወምም ኦነግ የጋራ ትግላችን አባልና ክንድ አንዲሆን ከመጣር ኢሕአፓ አልቶጠበም።

ኦነግ በወያኔ ፀረ ኦሮሞነትና ፀረ ዴሞክራሲያዊነት ተገዶ ወደ ትጥቅ ትግል ስላመራም ኢሕአፓ ሊያወግዘው አልቃጣም:: እንደ ነፃ ድርጅትም ኦነግ አጋሬ ማነው ለሚለው ጥያቄ የመሰለውን መልስ ቢሰጥ ቢያንስ የሻዕቢያ ወዳጅ የነበረውና ከጠቀመው ከግራ ቀኙ ጋር የሚሰለፈው መለስ ዜናዊ ሊተቸው የሞራል ብቃት አለውም ብሎ አያምንም::

የኦሮሞ ሕዝብ በቁጥር ብዛት አንደኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው:: የኦሮሞ ሕዝብ በኢትዮጵያ ግንባታና ህልውና መስክ ከፍተኛ ሚናን የተጫወተና እየተጫወት የላም ሕዝብ ነው:: የኦሮሞ ሕዝብ መብቴ በአጠቃላይ ይከበር ብሎ የሚያካሂደው ትግል ደግሞ ፍትሃዊና የሚደገፍ፤ የኢትዮጵያን የዴሞክራሲ ትግል የሚያጎለብት ነው:: ለዚህም ነው ኢሕአፓ የኦሮሞን ሕዝብ ትግል ሙሉ በሙሉ የሚደግፈውና ከሀገራዊ ትግል የሚነጥለውን አቅዋም በመቃወም ለኢትዮጵያ በአንድነት እንታገል ሲል ደግሞ ደጋግሞ ጥሪ የሚያሰማው:: የሕዝብ መብትና እኩልነት ተሰርዞ አንድነት ዘበት ነው:: ለጭቆና ደግሞ መፍትሄው መገንጠል አይደለም:: ወያኔ የጭቁን ብሄረሰቦች አዛኝ ደጋፊ መስሎ አንቀፅ 39 ም ደንግጎ ቢሰየምም በተጨባጭ ግን ፀረ መብት ፀረ ሕዝብነቱን አረጋግጧል:: በብሄረሰቦች ላይ በተለይም በአማራውና በኦሮሞው ወዘተ ላይ እያካሄደ ያለውም ዘመቻ የሚታይ ነው:: የአንዱ መመከራ ኬላው ቢብስ እንጂ ኦሮሞውም፤አማራውም፤ህዲያውም፤አኝዋኩም፤ ሶማሌውም ወዘተተ ሁሉም የመለስ ዜናዊን አገዛዝ የግፍ ጅራፍ እየቀመሰ ነው:: አብሮ በጋራ መታገልና የጋራ ሀገርን ማዳን የሚያስፈልገው ለዚህ ነው:: ኢትዮጵያ ከማንም ባላነስ የኦሮሞ ሕዝብ ሀገር ናት:: ደምቶላታል:: ቢበደልም ሀገሬ ብሎ ሞቶሏታል:: ይህን መስዋዕትነቱን መና ማስቀረትና ሚናውንና ታሪካዊ ቦታውን መሰረዝ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነቱ ለምበቱ መታገል ነው ያለበት:: የኦሮሞ ሕዝበ እያደረገ ያለው ይህኑ ነው:: ድርጅቶቹ ነን የሚሉት ሊከተሉት ድፍረቱ ሊኖራቸው ይገባል::

ኢሕአፓ በተጨባጭ ከኦሮሞ ሕዝብ ጎን የሚቆመው በመርህና በእምነቱ መሰረት ሲሆን ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ መብት ካልተከበረ የሀገርን ህሀልወና ማረጋገጥ ከቶም እንደማይቻል በማወቁ ነው::

የኦሮሞ ሕዘባችንን ፍትሃዊ ትግል ሙሉ ድጋፍ እንስጠው::